


# የዲሞክራሲ መጥበብ፣ የሁከት መጨመር

**የ2023 የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች**

#KeepItOn

# #KeepItOn

ከዚህ በታች የቀረበው ሪፖርት በ2023 የደረሱ የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶችን በተመለከተ #KeepItOn ካወጣው ዘገባ ላይ የተቀነጨበ ትርጉም ሥራ ነው። ሙሉ ዘገባውን https://www.accessnow.org/keepiton-2023-report ላይ ያገኛሉ።

**#KeepItOn** የኢንተርኔት መዘጋትን ለማስቆም ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችንና ጥረቶችን የማደራጀትና የማስተባበር ሥራዎችን የሚያከናውን ዘመቻ። ዘመቻው በሲሊከን ቫሊ በሚገኘው ራይትስኮን አማካኝነት በአገራችን የዘመን ቀመር በ2008 ወደ 70 በሚጠጉ የድርጅቶች ጥምረት የተጀመረ ነው። የጥምረቱ አባላት ቁጥር በፍጥነት ያደገ ሲሆን በዓለም ዙሪያ ከሚገኙ 106 ሀገራት የተውጣጡ ከ334 በላይ አባላት ይገኙበታል። አባላቱ ከሲቪል ማኅበረሰብና ከመብት ተሟጋች ቡድኖች እስከ የምርምር ማዕከላት፣ የክትትል መረቦች፣ ፋውንዴሽኖችና የሚዲያ ተቋማት የተውጣጡ ናቸው።

ይህ ሪፖርት ለ#KeepItOn ጥምረት በአክሰስ ናው የተዘጋጀ ሕትመት ሲሆን ዛክ ሮሰን፣ ፌሊሺያ አንቶኒዮና ካሮሊን ታኬት ከአክሰስ ናው ቡድን ጋር በመተባበር ጽፈውታል።

ደራሲዎቹ በተለዩ ዶና ዌንትወርዝ፣ አንጄላ አላርኮን፣ ብሪጅት አንድሬ፣ ጎልዳ ቤንጃሚን፣ ራማን ጂት ሲንግ ቼማ፣ ጁሊዮ ኮፒ፣ ማርዋ ፋታፍታ፣ ኦሴይ ማኑ ካጊያህ፣ ናታሊያ ክራፒቫ፣ ጂዩሚ ኮኮንዩ፣ ናምራታ ማሄሽዋሪ፣ ፒተር ሚሴክ፣ ካሴም ምኔጃ፣ ዋዩ ፊዮ ማይንት፣ ሽሩቲ ናራያን፣ ላውራ ኦብሪየን፣ ናሮ ኦሞ-ኦሳጊ፣ ጋስፐር ፒሳኑ፣ ፕራቲክ፣ አሌክሲያ ስኮክ፣ ቫካው፣ አዩመን ዛግዱዳና አናስታሲያ ዝሂርሞንትን ላበረከቱት አስተዋፅዖ ማመስገን ይፈልጋሉ። በተጨማሪም አድቮከሲ አሴምብሊ ሽትዳውን አካዳሚ፣ አታን፣ ክላውድፍሌር፣ ዲጂታሊ ራይት፣ ኢንተርኔት አውቴጅ ዲቴክሽን ኤንድ አናሊሲስ፣ ኬንቲክ፣ ሚያን ግሩፕ፣ የሚያንማር ኢንተርኔት ፕሮጀክት፣ ኦፕን ኦብዘርቫቶሪ ኦብ ኔትወርክ ኢንተርፌስ፣ የህንድ የሶፍትዌር ነፃነት ሕግ ማእከልና ሌሎች የ#KeepItOn ጥምረት አባላት ላበረከቱት ጠቃሚ መረጃና አስተያየት እንዲሁም መረጃዎችንና ምንጮችን በመመርመር ለዚህ ሪፖርት ላበረከቱት አስተዋፅዖ ማመስገን እንፈልጋለን። ማናቸውም ስሕተቶች፣ የተሳሳቱ መግለጫዎች ወይም ግድፈቶች ቢኖሩ የኛ ብቻ መሆኑን እየገለጽን የሚኖራችሁን አስተያየት በደስታ የምንቀበል መሆናችንን ለመጠቆም እንወዳለን።

ዲዛይንና ሥዕላዊ መረጃ ሎረን ጆርዳኖና ሴጅ ቼንግ።

## ስለመረጃችን ማስታወሻ

ይህ የ#KeepItOn ሪፖርት የአክሰስ ናው እና #KeepItOn ጥምረት በ2023 የመዘገባቸውን የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች ይመለከታል። በሪፖርቱ ጠቅለል ያለ መረጃ ለመስጠት የምንሞክር ሲሆን መረጃው በቴክኒካል ልኬትና እንደ ዜናዎች ወይም የግል ገጠመኞች ባሉ ዐውዳዊ መረጃዎች ላይ የተመሠረተ ነው። የምንጠቀመው ዘዴ ከሚገጥሙት ውስንነቶች መካከል ሪፖርት ያልተደረጉ የኢንተርኔት መዘጋት ጉዳዮች ሊኖሩ መቻላቸው አንዱ ሲሆን አኃዞቹ ከሕትመት በኋላ አዲስ መረጃ ሲገኝ/ከተገኘ ሊለወጡ ይችላሉ።
በ2023 ዓ.ም ከቀደምት ዓመታት ወደ መረጃ ቋት ስለገቡት የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች ግንዛቤ ማግኘት የተቻለ ሲሆን እነዚህን ለውጦች የተመለከቱ መዛግብቶችን ወደ STOP መረጃ ቋት https://accessnow.org/keepiton-data በመግባት ማግኘት ይቻላል። ከታች ያሉት ሁሉም መረጃዎች ሪፖርቱ ከታተመበት ጀምሮ ያለውን የመጨረሻ ወቅታዊ መረጃ ያሳያሉ።

እኛ ስለምንጠቀመው ዘዴ፣ በተደጋጋሚ ስለየሚጠየቁ ጥያቄዎችና በቀጣይ ስለሚሠሩ ሥራዎች አዳዲስ መረጃዎችን ለማግኘት https://accessnow.org/keepiton-data-methodologyን ይጎብኙ።


ግንቦት 2024

CC BY

## ሀ/ በ2023 ዓ.ም የደረሱ የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች፡- ዓለም አቀፍ እይታ

# የ2023 መረጃ አጠቃላዩ እይታ


### የተመዘገቡ የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች *




* እነዚህ አኃዞች ይህ ሪፖርት በወጣበት ወቅት ያለውን የቅርብ ጊዜ መረጃ የሚያሳዩ ሲሆን  ከዚህ ቀደም ለነበሩት ዓመታት የታተሙ ሪፖርቶች ላይ አጠቃላዩ አዳዲስ መረጃዎች ተካተዋል።

### የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች የደረሱባቸው አገሮች ብዛት

| 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | 2023 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 27 | 23 | 28 | 36 | 34 | 39 | 40 | 39 |



**ህንድ:- 116**
**ሚያንማር፡- 37**
**ኢራን፡- 34**
**ፍልስጤም፡-16 ****
**ዩክሬን፡- 8 ****
**ፓኪስታን፡- 7**
**ኢራቅ፡- 6**
**አዘርባጃን፡- 5**
**ኢትዮጵያ፡- 4**
**ሴኔጋል፡- 4**

ባንግላዲሽ፡- 3
ሩሲያ:- 3
ዮርዳኖስ፡- 3
ሊቢያ:- 3
ቻይና: - 2
ጊኒ፡- 2
ሞሪታንያ፡- 2
ኦማን፡- 2
ታንዛንያ፡- 2
ቱርክሜኒስታን: 2

ሱዳን፡- 2
ሶርያ፡- 2
ቱርኪዬ:- 2
አልጄሪያ፡- 1
ብራዚል፡- 1
ኩባ፡- 1
ጋቦን፡- 1
ኢንዶኔዠያ፡- 1
ኬንያ፡- 1
ሊባኖስ፡- 1

ሞዛምቢክ፡- 1
ኔፓል፡- 1
ኳታር፡- 1
ሳዑዲ አረቢያ፡- 1
ሶማሊላንድ፡- 1
ሱሪናም፡- 1
የተባበሩት ዓረብ ኢምሬቶች:-1
ዩጋንዳ:- 1
ቬንዙዌላ፡- 1

** በፍልስጤምና በዩክሬን የደረሱት የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች በውጭ አካላት ምክንያት የደረሱ ናቸው።

# የ2023 የኢንተርኔት መዘጋት መነሻ ምክንያቶች

| ግጭቶች | ተቃውሞዎች | ፈተና | ምርጫ |
|---|---|---|---|
| በግጭት ወቅት በ**9** ሀገራት የደረሱ **74** የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች | በተቃውሞዎች ወቅት በ**15** ሀገራት የደረሱ **63** የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች | የፈተና ኩረጃን ለመከላከል" በ**6** ሀገራት የደረሱ **12** የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች | ከምርጫ ጋር በተያያዘ **5** አገራት ውስጥ የደረሱ **5** የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች |
| 2023: 74 | 2023: 63 | 2023: 12 | 2023: 5 |
| 2022: 36 | 2022: 63 | 2022: 8 | 2022: 5 |
| 2021: 19 | 2021: 39 | 2021: 11 | 2021: 7 |
| 2020: 15 | 2020: 16 | 2020: 8 | 2020: 10 |
| 2019: 52 | 2019: 65 | 2019: 8 | 2019: 12 |
| 2018: 2 | 2018: 45 | 2018: 11 | 2018: 12 |
| 2017: 3 | 2017: 37 | 2017: 7 | 2017: 6 |
| 2016: 3 | 2016: 27 | 2016: 6 | 2016: 5 |

**በ2023 የታየ የኢንተርኔት መዘጋት መነሻ ምክንያት፡-**

**የተፈጥሮ አደጋዎች**

በተፈጥሮ አደጋዎች ወቅት በ**4** ሀገራት የደረሱ **4** የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች

# የ2023 የኢንተርኔት መዘጋት አዝማሚያዎች

1. **የኢንተርኔት መዘጋት ከባባድ የሰብአዊ መብት ረገጣዎችንና ጥቃቶችን ለመሸፈኛነት መዋሉ እንደቀጠለ ነው።**

| | |
|---|---|
| በ**11** ሀገራት የደረሱት **51** የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች ከተመዘገቡት ከባባድ የሰብአዊ መብት ረገጣዎች ጋር የሚገናኙ ናቸው *** | አዘርባጃን፣ ኢትዮጵያ፣ ኢራን፣ ዮርዳኖስ፣ ሞሪታንያ፣ ሚያንማር፣ ፍልስጤም፣ ሩሲያ፣ ሶማሊላንድ፣ ሱዳን፣ ዩክሬን |

*** ከባባድ የሰብአዊ መብት ረገጣዎች ግድያን፣ ማሠቃየትን፣ አስገድዶ መድፈርን ወይም በመንግሥት፣ በወታደሮችና በፖሊስ ወይም በጸጥታ ኃይሎች የሚፈጸሙ የጦር ወንጀሎችን ጨምሮ የጥቃት ማስረጃዎች ያሉባቸውን ጉዳዮች ያጠቃልላል።

2. **ባለሥልጣናት የኢንተርኔት መዘጋትን እንደ መደበኛ ሁኔታ ከመቁጠር መቆጠብ አለባቸው**

በ2023 በ**25** ሀገራት **53** የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች፣ በ2022 ደግሞ በ**29** ሀገራት **39** የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች

| | |
|---|---|
| ግሪንደር (Grindr) ከፌስቡክ ቀጥሎ ከህንድ ውጭ ሁለተኛው በጣም የተዘጋው የዲጂታል መገናኛ አውታር ሲሆን ተጽእኖው በ12 ሀገራት የሚገኙ ሰዎችን የነካ ሲሆን የLGBTQ+ መገናኛዎች ላይ አነጣጥሯል። | ቻይና፣ ኢንዶኔዥያ፣ ኢራን፣ ዮርዳኖስ፣ ሊባኖስ፣ ኦማን፣ ፓኪስታን፣ ኳታር፣ ሳዑዲ አረቢያ፣ ታንዛኒያ፣ ቱርኪዬ፣ የተባበሩት ዓረብ ኢምሬቶች |

## 3. እጅግ የከፋ ሕገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዎች የኢንተርኔት መዘጋትን እንደመሸሸጊያ የሚጠቀሙ ሲሆን ለወንጀል ድርጊታቸውም ማበረታቻ ይሆናቸዋል።

ከጥቅምት 25፣ 2013 ጀምሮ **1,153** ቀናት ****
በትግራይ፣ ኢትዮጵያ

ከነሐሴ 2013 ጀምሮ **864** ቀናት ****
በመሳ ሚያንማር በደርዘን በሚቆጠሩ የከተማዋ ክፍሎች

ከየካቲት 2014 ጀምሮ **694** ቀናት ****
በፓንጅጉር፣ ፓኪስታን

ከ2023 እስከ 2024 ድረስ **35** የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች እንደቀጠሉ ነው።
በ2023 በ**17** ሀገራት ውስጥ ሰዎች **ዓመቱን ሙሉ** የኢንተርኔት መዘጋት ደርሶባቸዋል።

**** ከታኅሣሥ 21፣ 2016 ጀምሮ ያለው የቀናት ብዛት

## 4. የኢንተርኔት መዘጋት የሚደርስባቸው ቦታዎች ስፋት እየጨመረ ነው።

በ2023 ከደረሱት ሁሉም የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች ውስጥ **30.4%** ብቻ በአነስተኛ ደረጃ ላይ የነበሩ (በአንድ ከተማ፣ ክልል ወይም መንደር ላይ ብቻ ተጽዕኖ የነበራቸው) ሲሆን በ2022 **46.8%** የሚሆኑት ሁሉም የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች በአነስተኛ ደረጃ ላይ ነበሩ።

**80** የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች በበርካታ ክልሎች ወይም በመላው ሀገሪቱ ላይ ተፅዕኖ አሳድረው የነበረ ሲሆን ይህም ከአውሮፓውያኑ 2016 ጀምሮ የተመዘገበ ከፍተኛው የመዘጋት ቁጥር ነው።

### ከ2016 ጀምሮ

በዓለም ዙሪያ
**1,458**
የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች አጋጥመዋል

**82**
ሀገራት ተጽእኖ ደርሶባቸዋል

ከ106 ሀገራት የተውጣጡ
**334** የ#KeepItOn ጥምረት አባላት

### በ2023 ኢንተርኔት የዘጉ አዳዲስ ሀገራት

**ኬንያ *****
**ሞዛምቢክ**
**ኔፓል**
**ሱሪናም**

***** ይህ በኬንያ መንግሥት የተፈጸመ የመጀመሪያው የኢንተርኔት መዘጋት ክስተት ሲሆን ከዚህ ቀደም በጎርጎሮሳውያኑ 2020 ደርሰው የነበሩት አገዳዎች በሦስተኛ ወገን የተጣሉ ነበሩ።

**ሊባኖስ**
**ኳታር**
**የተባበሩት ዓረብ ኢምሬቶች**
በSTOP የመረጃ ቋት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመዘገቡ የመገናኛ አውታሮችን ለበርካታ ዓመታት የዘጉ ሀገራት

# የ2023 የአፍሪካ ቀጣናዊ መግለጫ

| 2021 | 2022 | 2023 |
| --- | --- | --- |
| 19 መዘጋት ክስተቶች | 9 መዘጋት ክስተቶች | 17 መዘጋት ክስተቶች |
| በ12 ሀገራት | በ7 ሀገራት | በ9 ሀገራት |

**ኢትዮጵያ: 4**

**ሴኔጋል: 4**

ጊኒ: **2** ታንዛኒያ: **2**
ጋቦን: **1** ሱማሊላንድ: **1** ኡጋንዳ: **1**

## ለመጀመሪያ ጊዜ የዘጉ፡-

ኬንያ: **1**
ሞዛምቢክ: **1**

**2022** 44.5%
**2023** 58.8%

በነዚህ ሀገራት 58.8% የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች ከተቃውሞዎች ጋር የተገናኙ ናቸው ፡-

ሴኔጋል፡- 4 ኢትዮጵያ፡- 2 ጋቦን፡- 1 ጊኒ፡- 1
ሞዛምቢክ፡- 1 ሶማሊላንድ፡- 1

33.3%
58.8%

በነዚህ ሀገራት 58.8% የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች በመገናኛ ዘዴዎች ላይ ያነጣጠሩ ናቸው፡-

ኢትዮጵያ፡- 2 ጊኒ፡- 2 ሴኔጋል፡- 2 ታንዛኒያ፡- 2 ኬንያ፡- 1
ዩጋንዳ፡- 1

በ2023 የኢንተርኔት መዘጋት በአፍሪካ እንደገና የታየ ሲሆን በ**9** ሀገራት ውስጥ **17** የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች ተመዝግበዋል። ይህም በ2022 በ**ሰባት** ሀገራት ውስጥ ከተከሰተው **ዘጠኝ** የኢንተርኔት መዘጋት እጥፍ እንደማለት ነው። በ2023 የታየው ይህ ከፍተኛ እድገት ኢንተርኔት መዘጋትን በቀጣናው እንደ አንድ የአፈና መሣሪያነት የመጠቀም ሁኔታ አለ ብለን እንድንሞግት የሚያደርግ ነው።

በአፍሪካ አጠቃላይ የሰብአዊ መብት ሁኔታ እየሸቀለቀለ ባለበት በዚህ ወቅት.[1] መንግሥታት ተቃውሞዎች፣ ምርጫዎች፣ ብሔራዊ ፈተናዎችና ግጭቶች በሚኖሩበት ወቅት እገዳዎችን ሲጥሉ ተስተውሏል። ዓላማው **የሐሳብ ልዩነትን ማጥፋትና የመረጃ ፍሰትን መከልከል ነው።**

2021 ቀጣናው በአስደንጋጭ ሁኔታ በ**ሰባት** ሀገራት የመጀመሪያውን የኢንተርኔት መዘጋት ክስተት ያስተናገደበት ዓመት ቢሆንም 2022 በዚህ ረገድ እፎይታ ታይቶበታል። በዚያ ዓመት የኢንተርኔት እገዳ የጣሉ ሀገራት ዝርዝር ውስጥ የገባ የቀጣናው ሀገር አልነበረም። በሚያሳዝን ሁኔታ በ2023 ኢንተርኔት ላይ እገዳ የጣሉ **ሁለት** አዳዲስ አገራት ብቅ አሉ። ሞዛምቢክ ከአካባቢ ምርጫዎች_[2]_ጋር በተያያዘ የተነሡትን ተቃውሞዎች በኃይል ለማስቆም የሞባይል ኔትወርኮችን አቋረጠች። ኬንያ ደግሞ በብሔራዊ ፈተና[3] ወቅት ቴሌግራምን አገደች። ይህም ሀገሪቱ ባለፈው ዓመት በተደረገው ምርጫ የመገናኛ አውታሮችን ላለማገድ የገባችውን መሐላ የቀለበሰ ነበር።[4]

እነዚህ ማነቆዎች እንደተጠበቁ ሆኖ 2023 ሲወደሱ የሚገባቸው መልካም ለውጦች የታዩበት ዓመት ነበረ። የዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ

1. Freedom House (2024). NEW REPORT: Africa Marks a Decade of Decline in Freedom, with 2023 Being Marred by Electoral Violence and Civil Conflict. https://freedomhouse.org/article/new-report-africa-marks-decade-decline-freedom-2023-beingmarred-electoral-violence-and/
2. 2 Club of Mozambique (2023). CIP Mozambique Elections: Internet cut, counting starts. https://clubofmozambique.com/news/cip-mozambique-elections-internet-cut-counting-starts-246517/
3. 3 Access Now (2023). Open letter: clarification on Telegram blocking in Kenya. https://www.accessnow.org/press-release/openletter-clarification-on-telegram-blocking-in-kenya/
4. 4 Access Now (2023). Warning: blocking online platforms in Kenya will spread election disinformation. https://www.accessnow.org/press-release/kenya-online-platforms-social-media-blocking-internet-shutdown-election/

ኮንጎ፣ ናይጄሪያና ሴራሊዮን ባለሥልጣናት በምርጫ ወቅት የኢንተርኔት አገልግሎትን ላለማቋረጥ የገቡትን ቃል ጠብቀው ተገኙ። ከምርጫ ጋር በተያያዘ የሚደረግ የኢንተርኔት መዘጋት በዲሞክራሲ ላይ ከሚያሳድረው ከፍተኛ ተጽእኖ አኳያ ሲታይ ይህ ትልቅ ትርጉም ያለው እርምጃ ነው። [5]

በአፍሪካ በምርጫ ወቅት የሚደረግ የኢንተርኔት መዘጋት ላይ በተደረገው የሕግ ትግል አበረታች ለውጦችን ተመልክተናል። በ2023 የምዕራብ አፍሪካ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ (ኢኮዋስ) የፍትሕ ፍርድ ቤት በ2020 የጊኒ ሕገ-መንግሥታዊ ሕዝበ ውሳኔና አጠቃላይ ምርጫ በተካሄደበት ወቅት የተደረገው የኢንተርኔት መዘጋት ሕገ-ወጥ መሆኑን በማወጅና በመቃወም የዳኝነት ሥልጣኑን አሳይቷል።[6]

## በተቃውሞ፣ በፖለቲካ አለመረጋጋትና በብጥብጥ ወቅት የሚደረግ የኢንተርኔት መዘጋት

ቀጣናው በ2023 በኢኮኖሚ ችግር፣ በዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ማሽቆልቆልና በፖለቲካ አለመረጋጋት ምክንያት በተነሡ መጠነ ሰፊ ተቃውሞዎች ክፉኛ ተመቶ ነበር። ለእነዚህ ተቃውሞዎችና የፖለቲካ አለመረጋጋት ምላሽ ለመስጠት ባለሥልጣናት ኢንተርኔትን **10** ጊዜ ዘግተዋል። ይህም ለሦስተኛ ተከታታይ ዓመት ተቃውሞዎች በአፍሪካ ኢንተርኔት እንዲዘጋ የሚያደርጉ ግንባር ቀደም ምክንያት እንዲሆኑ አድርጓል።

በብዙ ተቃውሞዎችና የፖለቲካ አለመረጋጋት መመሰቃቀል የደረሰባቸው የሴኔጋል ባለሥልጣናት የኢንተርኔት አገልግሎትን ለማቋረጥ ወይም የመገናኛ አውታሮችን አራት ጊዜ ለመዘጋት ተገደዋል። የተቃዋሚ መሪ የሆኑት ኡስማን ሶንኮ መታሰርን ተከትሎ በዳካርና ዚጊንኮር ግንቦት 24 ቀን ተቃውሞዎች ከተቀሰቀሱ በኋላ ባለሥልጣናት ዋትሳፕን፣ ቴሌግራምን፣ ኢንስታግራምን፣ ኢክስን (የቀድሞው ተዊተር) እና የትዩብን[7] ጨምሮ የማኅበራዊ ሚዲያ አውታሮችን አገዱ። ከሦስት ቀናት በኋላ ባለሥልጣናቱ አገዳው የሞባይል ኢንተርኔት አገልግሎትንም እንዲያካትት አደረጉ።[8]

ሶንኮ በአገሪትን አቆጣጠር ሐምሌ 21 ቀን 2015 በድጋሚ ለእስር ተዳረገ። የሶንኮን እስር ተከትሎ ሕዝባዊ ተቃውሞዎች እንደገና ሲያገረሹ ባለሥልጣናቱ ሁኔታውን በኃይል ለማስቆም በወሰዱት እርምጃ የሞባይል ኢንተርኔት አገልግሎት እንዲቋረጥ ያደረጉ ሲሆን ተክቶክን[9] ሙሉ በሙሉ አገዱ። ምንም እንኳን ባለሥልጣናቱ ከሐምሌ 29 ቀን ጀምሮ የሞባይል ኢንተርኔት አገልግሎት እንደገና እንዲጀምር ያደረጉ ቢሆንም እስከ የካቲት ወር 2016 ዓ.ም ድረስ ያለምንም ማብራሪያ ተክቶክ ላይ የተጣለው እገዳ እንዲቀጥል አድርገዋል።[10]

የሴኔጋል መንግሥት ኢንተርኔት መዘጋት ያስፈለገው "ጥላቻ አዘልና ግጭት ቀስቃሽ መልእክቶች" እንዳይሰራጩ ለማገድ መሆኑን ለማስረዳት የሞከረ ሲሆን ለተፈጠሩት ብጥብጦች ዲጂታል የመገናኛ አውታሮችን ተጠያቂ አድርጓል[11]። ሶንኮ መጀመሪያ ላይ በአውሮፓውያኑ 2021 ከታሰረ በኋላ ሕዝባዊ ተቃውሞዎችን ለማስቆም መንግሥት ከዚህ ቀደም እገዳዎችን አድርጎ ነበር[12]። መንግሥት ላይ የሚደርሱ ትችቶችን ለማፈን በተደጋጋሚ የተደረገው ይህ ኢንተርኔትን የማስተጓጎል አካሄድ ጋዜጠኞች ላይ ከሚደርሰው እስርና የቀድሞ ፕሬዝዳንት ማኪ ሳል በማኅበራዊ ሚዲያ አውታሮች ላይ ቁጥጥር የሚያደርግ አዲስ ሕግ እንዲወጣ ካደረጉት ግፊት ጋር ሲደመር ወደ ዲጂታል አምባገነንነት እየተሄደ ለመሆኑ የማስጠንቀቂያ ደወል ነው[13]። ከዚህ ውጥረት ከሰፈነበት የምርጫ ዑደት በኋላ በየካቲትና መጋቢት 2016 ዓ.ም አዲስ አስተዳደር ሲመጣ የሴኔጋል ባለሥልጣናት ለ#KeepItOn ያላቸውን ቁርጠኝነት ያረጋግጡ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።[14]

5. Access Now (2023). 2023 elections and internet shutdowns watch. https://www.accessnow.org/campaign/2023-electionsand-internet-shutdowns-watch/; Actu7 (2023). Elections 2023: "On ne coupera pas la connexion internet le jour du vote" (PeterKazadi). https://actu7.cd/2023/12/19/elections-2023-on-ne-coupera-pas-la-connexion-internet-le-jour-du-vote-peter-kazadi/;Sahara Reporters (2023). Nigerian Communications Commission Says No Network Shutdown During General Elections. https://saharareporters.com/2023/02/24/nigerian-communications-commission-says-no-network-shutdown-during-generalelections/;Felicia Anthonio (@FelAnthonio). X post. 4:50 pm. June 29, 2023. https://x.com/FelAnthonio/status/1674460297715757080

6. Media Defence (2023). ECOWAS Court condemns internet shutdown in Guinea. https://www.mediadefence.org/news/ecowascourt-condemns-internet-shutdown-in-guinea/

7. Technext (2023). Senegal limits social media access following protests over sentencing of opposition leader.https://technext24.com/2023/06/03/sonko-senegal-social-media/

8. Reuters (2023). Senegal government cuts mobile internet access amid deadly rioting. https://www.reuters.com/world/africa/senegal-government-cuts-mobile-internet-access-amid-deadly-rioting-2023-06-04/

9. Reuters (2023). Senegal blocks TikTok in widening clampdown on dissent. https://www.reuters.com/world/africa/senegalsuspends-tiktok-saying-it-was-threatening-stability-2023-08-02/

10. Access Now (2023). Stop the internet shutdowns: Senegal authorities must end censorship. https://www.accessnow.org/press-release/internet-shutdowns-senegal/; Africanews (2023). Senegal declines to lift TikTok ban. https://www.africanews.com/2023/10/06/senegal-declines-to-lift-tiktok-ban/

11. News24 (2023). Senegal shuts down internet as riots erupt after opposition leader sentenced for sex crime. https://www.news24.com/news24/africa/news/senegal-shuts-down-internet-as-riots-erupt-after-opposition-leader-sentenced-for-sexcrime-20230602/

12. Bloomberg (2021). Senegal Shuts Down TV Stations, Internet Disrupted Amid Protests. https://www.bloomberg.com/news/articles/2021-03-05/senegal-shuts-down-tv-stations-internet-disrupted-amid-protests/

13. The Africa Report (2021). Senegal's president joins the chorus against Twitter and Facebook.https://www.theafricareport.com/99491/senegals-president-joins-the-chorus-against-twitter-and-facebook/;Media Foundation for West Africa (2024). Senegal: Six journalists arrested over Minister's defamation complaint. https://www.mfwa.org/issues-in-focus/senegal-six-journalists-arrested-over-ministers-defamation-complaint/

14. Al Jazeera (2024). Senegal's top court confirms Bassirou Diomaye Faye's election victory. https://www.aljazeera.com/news/2024/3/29/senegals-top-court-confirms-bassirou-diomaye-fayes-election-victory/

በጎርጎሮሳውያኑ 2021 ወታደራዊው ጁንታ የአልፋ ኮንዴ መንግሥትን ካስወገደ በኋላ በጊኒ ያለው የፕሬስ ነፃነትና የሰብአዊ መብት ሁኔታ በከፍተኛ ሁኔታ ተባባሰ።[15] በአገራችን የዘመን ቀመር በግንቦት ወር 2015 ጁንታው ላይ የሲቪል ማኅበረሰቦች ተቃውሞ ሲበረታ ወታደራዊው ኃይል ዋትስአፕ፣ ፌስቡክ፣ ሜሲንጀር፣ ቴሌግራም፣ ስናፕቻፕና ኢንስታግራምን የመጠቀም መብት ላይ ለበርካታ ወራት ገደብ ጣለ።[16] ወታደራዊው ኃይል ለመገናኛ አውታሮች መቋረጥ አጿ እንደሌለበት በመግለጽ ጊኒን ከኢንተርኔት ጋር የሚያገናኘው የባሕር ውስጥ ገመድ (ኬብል) ላይ በደረሰ የቴክኒክ ችግር ምክንያት[17] መሆኑን ቢስረዳም ኦፕን ኦብዘርቫቶሪ ኦቭ ኔትወርክ ኢንተርፌስ(OONI) የሰበሰበው መረጃ አገዳው ሆን ተብሎ (በቲኤል ኤስ ኢንተርፌረንስ) የተደረገ መሆኑን ያመለክታል።[18] ጁንታው በኅዳር ወር መጠነ ሰፊ መገናኛ አውታሮችን የመዘጋት እርምጃ ወሰደ። የሬዲዮ ጣቢያ ማስተላለፊያዎችን ዘጋ፣ የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን አገደ እንዲሁም የማኅበራዊ ሚዲያ አውታሮችን ሙሉ በሙሉ ዘጋ።[19] በአገራችን የዘመን አቆጣጠር የካቲት 14 ቀን 2016 ነበር እኒህ የመገናኛ አውታሮች እንዲመለሱ የተደረገው።[20]

ግጭት ያለማቋረጥ በሚቀሰቀስባትና የተለያዩ የትግራይ ክፍሎች ለዓመታት ከግንኙነት በተቋረጡባት ኢትዮጵያ ባለሥልጣናቱ ለሀገራዊ ቀውሶች ምላሽ ለመስጠት ኢንተርኔት መዝጋት እንደ አማራጭ መውሰዳቸውን ቀጥለውበታል። የካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች የተቃውሞ ጥሪ ማቅረባቸውን ተከትሎ መንግሥት ፌስቡክን፣ ቲክቶክንና ቴሌግራምን ጨምሮ የማኅበራዊ ሚዲያ አውታሮች ላይ ክልከላ የጣለ ሲሆን አገዳው ከአምስት ወራት በላይ ቆይቷል።[21] የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት ተቃውሞው ሕገ-ወጥ እንደሆነና ሕዝቡም እንዳይሰተፍ የገለጹ ሲሆን ሁኔታው ብጥብጥ ሊፈጥር እንደሚችል አስጠንቅቀዋል።[22]

በመጨረሻም የሞሪታኒያ ባለሥልጣናት በሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር "አሸባሪዎች" ተብለው የተፈረጁ አራት እስረኞች በኑዋክቾት ከሚገኝ እስር ቤት ማምለጣቸውን ተከትሎ የሞባይል ኢንተርኔት አገልግሎት የካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም እንዲታገድ አደረጉ።[23] ባለሥልጣናቱ እስረኞቹን በአገር አቀፍ ደረጃ የማፈላለግ ሥራ በሚያከናውኑበት ወቅት ሰዎች የሞባይል ኢንተርኔት አገልግሎት ማግኘት አልቻሉም ነበር። ይህም ደኅንነታቸው አደጋ ላይ እንዲወድቅ አድርጓል።[24] ይህ በ2023 በዓለም አቀፍ ደረጃ ከእስር ቤት ማምለጥ ጋር በተያያዘ ምላሽ ለመስጠት ከተደረጉ በርካታ የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች ውስጥ አንዱ ነው። በሕግ አስከባሪ አካላት የሚደረገው ይህ የቁጥጥር ዘዴ አሳሳቢ ነው።

## በምርጫ ወቅት የሚደረጉ የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች

በጎርጎሮሳውያኑ 2022 ከታየው አንጻራዊ ጸጥታ ከሰፈነበት የምርጫ ዓመት በኋላ አክሰስ ናው በ2023 ኢንተርኔትን የዘጉ 11 የአፍሪካ ሀገራትን በ#KeepItOn ኢሌክሽን ዋች ዝርዝር ውስጥ አስቀምጧል። እነሱም ቤኒን፣ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ፣ ኢስዋቲኒ፣ ጋቦን፣ ላይቤሪያ፣ ናይጄሪያ፣ ሴራሊዮንና ዚምባብዌ ናቸው።[25]

በዋችሊስት ዝርዝር ውስጥ ካሉት ሀገራት ጋቦን ብቻ ነበረች በኢንተርኔት አገልግሎት ላይ እገዳ የጣለችው። ነገር ግን ቀደም ብለን እንደገለጽነው ሞዛምቢክ በአካባቢያዊ ምርጫ ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ እገዳ ጥላለች። ከ2021 ምርጫ በኋላ እንዳደረገችው ሁሉ የጋንዳ ፌስቡክን ማገዷን ቀጥላለች። ይህም በአፍሪካ ከምርጫ ጋር በተያያዘ ምክንያት የተመዘገቡ የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶችን አጠቃላይ ብዛት ሦስት አድርሶታል።

15. Reporters Without Borders (2023). Unprecedented press freedom violations by Guinea military junta. https://rsf.org/en/unprecedented-press-freedom-violations-guinea-s-military-junta/

16. Access Now (2023). Stop shutting down the internet in Guinea: authorities must #KeepItOn amidst protest. https://www.accessnow.org/press-release/stop-shutting-down-the-internet-guinea/

17. Guinéenews (2023). Perturbation de la connexion internet en Guinée: quand Ousmane Gaoual fait le faux-fuyant.https://guineenews.org/perturbation-de-la-connexion-internet-en-guinee-quand-ousmane-gaoual-fait-le-faux-fuyant/

18. Open Observatory of Network Interference (@OpenObservatory). X post. 10:18 am. May 22, 2023. https://x.com/ OpenObservatory/status/1660591036316499968; see also Access Now (2022). A taxonomy of internet shutdowns: the technologies behind network interference. https://www.accessnow.org/shutdown-taxonomy-report

19. Media Foundation for West Africa (2023). Radio airwaves jammed, social media blocked in Guinea.https://www.mfwa.org/issues-in-focus/radio-airwaves-jammed-social-media-blocked-in-guinea/

20. Open Observatory of Network Interference (@OpenObservatory). X post. 3:23 pm. February 23, 2024.https://x.com/OpenObservatory/status/1761049064752177282/

21. Access Now (2023). Ethiopia authorities must stop blocking social media.https://www.accessnow.org/press-release/ethiopia-social-media-protest/

22. Addis Standard (2023). News: Joint Security, Intelligence Task Force cautions against unauthorized rallies, threatens to take actions as Orthodox Church Schism takes toll. https://addisstandard.com/news-joint-security-intelligence-task-force-cautions- against-unauthorized-rallies-threatens-to-take-action-calls-as-orthodox-church-schism-takes-toll/

23. Cloudflare Radar (@CloudflareRadar). X post. 8:19 am. March 6, 2023.https://x.com/CloudflareRadar/status/1632747652608581633/

24. Reuters (2023). Two guards killed in gunfire as four break out of jail.https://www.reuters.com/world/africa/two-guards-killed-gunfire-four-break-out-mauritania-jail-2023-03-06/

25. Supra note 5. Access Now (2023).

ከዚህ በፊት በተደረጉ ምርጫዎች ኢንተርኔትን ዘግቶ የነበረው በጋቦን የሚገኘው የአሊ ቦንጎ መንግሥት የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲቋረጥ አደረገ።[26] በተለያዩ የምርጫ ማእከላት የመራጮች አፈናና የምርጫ ሥነ-ምግባር መጓደል ስለመኖሩ ዘገባዎች በሚወጡበት በዚያ ሰዓት ነሐሴ 20 ቀን 2013 ዓ.ም ምርጫው ከተገባደደ በኋላ የምሽት ሰዓት እላፊ ታወጀ።[27] ከምርጫው በፊት ዓለም አቀፍ የምርጫ ታዛቢዎች አለመገኘታቸውና የውጭ የዜና ስርጭቶች መታገድ የምርጫውን ግልጽነትና ፍትሐዊነት ጥርጣሬ ውስጥ ያስገባ ነበር። የሚያስገርም ባይሆንም የጋቦን የምርጫ ማእከል ቦንጎ ማሸነፋቸውን ገለጸ። ይህም የፕሬዚዳንትነት ዘመናቸውን ለሦስተኛ ጊዜ ሊያራዝምላቸው የሚችል ነበር።[28] ሆኖም ወታደራዊው ኃይል መፈንቅለ መንግሥት በማድረግ የምርጫውን ውጤት ሻረው። የኢንተርኔት አገልግሎትም ወዲያው እንዲመለስ አደረገ። ይህ ለሦስት ቀን የቆየውን የኢንተርኔት መዘጋት እንዲያበቃ አደረገ።[29]

በሞዛምቢክ ደግሞ ባለሥልጣናቱ በወርኀ ጥቅምት የአካባቢ ምርጫዎች ላይ ለተሰሙት የተቃውሞ ድምፆች ምላሽ መስጠት ነበረባቸው። በመሆኑም በተቃዋሚዎች፣ በጋዜጠኞችና በሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ላይ የዘፈቀደ እስርና ግድያን የካተተ እርምጃ ወሰዱ።[30] የምርጫው ውጤት ይፋ መደረግ በመላ ሀገሪቱ ምርጫው ተጭበርብሯል[31] የሚል ሕዝባዊ ተቃውሞ እንዲነሣ አደረገ። ይህም በአኗ መዝገብ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ባለሥልጣናት የኢንተርኔት አገልግሎትን ያቋረጡበት ሆኖ ተመዘገበ። የኃይል መቆራረጥ ተከስቷል በሚልም የኢንተርኔት አገልግሎት ለሦስት ሰዓታት ያህል ተዘግቶ ቆየ።[32]

እነዚህ አቀባዎች በዲሞክራሲ ላይ እየደረሱ ያሉ አስከፊ ጥቃቶችን የሚያመለክቱ ናቸው። ነገር ግን ከላይ እንደገለጽነው ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ፣ ናይጄሪያና ሴራሊዮን ከዚህ በፊት ኢንተርኔት ላይ እገዳ ሲጥሉ የነበሩ ቢሆንም ሁሉም በምርጫ ወቅት የሰዎች ግንኙነት እንዳይቋረጥ ለማድረግ የገቡትን ቃል አጽንተዋል።[33] የአፍሪካ አገሮች በዚህ መንገድ በዓለም አቀፍ ደረጃ እገዳ ሲጥሉ ከነበሩ አገራት መካከል ቢሆኑም ወደ ለውጥ የሚደረገውን ጉዞ በግንባር ቀደም በመምራትም ቁርጠኝነታቸውን አሳይተዋል። ይህ ደግሞ ለቀጣናው ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሀገራትም አዎንታዊ ምሳሌ ነው። በአገራችን አቆጣጠር በወርኀ መጋቢት 2016 ሌላ መልካም ዜና ተሰማ። የአፍሪካ የሰብአዊና የሕዝቦች መብት ኮሚሽን (ACHPR) በአፍሪካ ውስጥ የሚታየውን በምርጫ ወቅት ኢንተርኔትን የመዝጋት ልምምድ የሚያወግዝ የአቋም መግለጫ አወጣ። ሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር የኢንተርኔት አገልግሎት አስፈላጊ ስለመሆኑ ወሳኝ የሆነ እውቅና ሰጠ። መንግሥታት በምርጫ ወቅት ሰዎች እርስ በርሳቸው እንዲገናኙ የሚያስችል እርምጃ እንዲወስዱ ጥሪውን አቀረበ።[34]

| እ.አ.አ. በ 2023 ከምርጫ ጋር በተያያዘ ኢንተርኔት አገልግሎትን የዘጉ የአፍሪካ አገሮች | እ.አ.አ. በ 2023 በምርጫ ወቅት ለ #KeepItOn የገቡትን ቃል ያጠፉ አገሮች |
|---|---|
| ጋቦን | ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ |
| ሞዛምቢክ | ናይጄሪያ |
| ኡጋንዳ | ሴራሊዮን |

26. 26 Reuters (2023). Gabon cuts internet, imposes curfew amid election voting delays. https://www.reuters.com/world/africa/gabon-vote-president-bongo-seeks-extend-56-year-family-dynasty-2023-08-26/27

27. Ibid.

28. 28 Reuters (2023). Gabon President Ali Bongo wins third term after disputed election. https://www.reuters.com/world/africa/gabon-president-ali-bongo-wins-third-term-after-disputed-election-2023-08-30/

29. 29 Reporters Without Borders (2024). Reacting to Gabonese army's post-coup statements, RSF issues ten recommendationsfor respecting press freedom. https://rsf.org/en/reacting-gabonese-army-s-post-coup-statements-rsf-issues-tenrecommendations-respecting-press/

30. 30 Club of Mozambique (2023). Mozambique: Shootings, arrests, internet and power outages taints vote counts, Sala da Pazsays. https://clubofmozambique.com/news/mozambique-shootings-arrests-internet-and-power-outages-taint-vote-countssala-da-paz-says-246532/

31. 31 ISS Africa (2023). Fraudulent municipal elections cripple democracy in Mozambique. https://issafrica.org/iss-today/fraudulent-municipal-elections-cripple-democracy-in-mozambique/

32. 32 allAfrica (2023). Mozambique: Internet Shutdown as Polls Close. https://allafrica.com/stories/202310120129.html/

33. 33 Supra note 5.

34. 34 African Commission on Human and Peoples' Rights (2024). Resolution on Internet Shutdowns and Elections in Africa - ACHPR.Res.580 (LXXVIII)2024. https://achpr.au.int/index.php/en/adopted-resolutions/580-internet-shutdowns-elections-africaachprres580-lxxvii/

## // በግጭት ወቅት የሚደረጉ የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች፡- ኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ መንግሥት የሚወስደው ኢንተርኔትን የመዝጋት እርምጃ በተለይ በግጭት ወቅት ጎጂ ነው። ሆኖም ሕዝባዊ ተቃውሞ ቢኖርም ባለሥልጣናቱ ሰዎች ሕይወታቸው አደጋ ላይ በሆነበት ወቅት ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ በጨለማ ውስጥ እንዲቆዩ ማድረጋቸውን እንደገፋበት ነው።

በሚያዝያ ወር 2015 ዓ.ም የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የአማራ ልዩ ኃይልንና ሌሎች የክልል አጋሮችን ትጥቅ ለማስፈታት ከተንቀሳቀሰ በኋላ በጎንደር፣ ቆቦ፣ ሰቆጣ፣ ወልድያና ሌሎች የአማራ ክልል ከተሞች ተቃውሞና ሁከት ተቀስቅሶ ነበር። ሁኔታው እየተባባሰ ሲሄድ የፌደራል ባለሥልጣናት በመላው የአማራ ክልል የሞባይል ኢንተርኔት አገልግሎት እንዲዘጋ በማድረጋቸው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ከሌላው ዓለም እንዲቆራረጡ ሆነ።[35] በነሐሴ ወር ግጭቱ ሲፋፋም መንግሥት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማወጅ ዘግናኝ የሆነ የዘር ማጽዳት መኖሩን የሚገልጹ ሪፖርቶች እየወጡ ባሉበት ሁኔታ የኢንተርኔት አገልግሎት እንደገና እንዲዘጋ አደረገ።[36] በተጨማሪም ባለሥልጣናቱ ጋዜጠኞችን በማሰርና የሚዲያ ተደራሽነትን በማገድ ስለሚካሄደው ግጭት ሽፋን እንዳይሰጥ የሚያደርግ እርምጃ ወሰዱ።[37]

ኢትዮጵያ በግጭት ወቅት የምትወስደው ስልታዊ የኢንተርኔት መዝጋትና የሚዲያ ሳንሱር እርምጃ ሰዎች የሕይወት አድን መረጃ እንዳያገኙ ከማድረጉም በሻገር የድንገተኛ ጤና እንክብካቤ፣ የውሃ፣ የምግብ፣ የመጠለያና የጥበቃ አገልግሎቶችን ጨምሮ ሰብአዊ እርዳታ ማግኘት እንዳይችሉ አጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ፈጠረ።[38] ይህ ኢንተርኔትን የማስተጓጎል ተግባር በተፋሳሚ ወገኖች እየተፈጸመ ያለውን ግፍና በደል ለማወቅና ለመመዝገብ የሚደረገውን ጥረት አስቸጋሪ ያደርገዋል።

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን በመንግሥት የጸጥታ አካላትና በመንግሥት ታጣቂዎች ከፍርድ ቤት ውጭ የተፈጸመ ግድያ፣ ጾታዊ ጥቃት፣ አካላዊ ጥቃት፣ መፈናቀልና የዜጎች ንብረት መውደሙን እንዲሁም ዘግናኝ የሆኑ የጾታና ጾታ-ተኮር ጥቃቶችን ጨምሮ እየተባባሰ በሄደው ግፍ ምክንያት አስከፊ ሁኔታ መፈጠሩን አስታውቋል።[39] ሪፖርቱ በታተመበት ጊዜ ከአንድ ዓመት በላይ ከቆየ ውጊያ በኋላ ግጭቱና በሰላማዊ ዜጎች ላይ የሚደርሰው ጥቃት ተባብሶ ቀጥሏል።[40] እነዚህ ግፎች ወደ ጦር ወንጀልነት ደረጃ ሲደርሱ የሚችሉ ሲሆን ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግን በእጅጉ የሚጥሱ ናቸው።[41]

ግጭት ከቆመ በኋላ እንኳን የኢንተርኔት መዘጋት በሰዎች ላይ የሚደርሰውን ሕመምና ሥቃይ የሚያባብስ ከመሆኑም በላይ ከጥቃትና ውድመት የማገገም ሂደቱን አስቸጋሪ ያደርገዋል። ይህን እየጻፍን ባለንበት ሰዓት በትግራይ ለዓመታት የዘለቀውን ግጭትና ሰብአዊ ቀውስ ተከትሎ በኅዳር 2014 ዓ.ም የተጀመረው የሰላም ሂደት እስካሁን ፍሬ አላፈራም።[42] የማያቋርጥ የጸጥታ ችግር፣ ድርቅ፣ ረኃብና የሰብአዊ እርዳታ መስተጓጎል ይስተዋላል። እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ከጦርነቱ በኋላ ሕይወታቸውን ለመግፋት በሚሞክሩ ሰላማዊ ሰዎች ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን ቀጥለዋል።[43] ቀድሞውንም በጥሩ ሁኔታ ላይ ባልነበረው የቴሌኮሙኒኬሽን መሠረተ ልማት ላይ ያጋጠሙት ያልተቋረጡ ጥቃቶችና በባለሥልጣናቱ ለመልሶ ግንባታ የተሰጠው አጥጋቢ ያልሆነ ምላሽ በትግራይ የሚኖሩ ብዙ ሰዎች ሙሉ በሙሉ ከግንኙነት እንዲቋረጡ አድርጓል። በተጨማሪም ኔትወርክ አግኝተው ከዘመድ አዝማድ ጋር ለመገናኘት ከሚኖሩበት ማኅበረሰብ ርቀት ለመሄድ ወይም እጅግ በጣም ቀርፋፋና አስተማማኝ ያልሆነ አገልግሎት ለመጠቀም ተገደዋል። ቀደም ብለን እንደ ገለጽነው በ2023 መገባደጃ ላይ ብዙዎች **1,153** ቀናትን ከግንኙነቶች ተቋርጠው ነበር ያሳለፋት የውም እርዳታን እጅግ በሚሹበት ወቅት።

35. The Guardian (2023). Gun battles erupt in Ethiopia as PM axes Amhara region's security force. https://www.theguardian.com/global-development/2023/apr/12/gun-battles-erupt-in-ethiopia-as-pm-axes-amhara-regions-security-force/

36. The Guardian (2023). Ethiopia declares a state of emergency in Amhara amid increasing violence. https://www.theguardian.com/global-development/2023/aug/04/ethiopia-declares-a-state-of-emergency-in-amhara-amidincreasing-violence/; OHCHR (2023). Comprehensive investigative findings and legal determinations. International Commission of Human Rights Experts on Ethiopia. https://www.ohchr.org/sites/default/files/documents/hrbodies/hrcouncil/chreetiopia/a-hrc-54-crp-3.pdf

37. Addis Standard (2023). News: CPJ urges authorities to release journalist detained without charge.https://addisstandard.com/news-cpj-urges-authorities-to-release-journalist-detained-without-charge/38

38. See supra note 36.

39. Ethiopian Human Rights Commission (2023). Amhara Region: Concerning human rights violations in the context of the armed conflict. https://ehrc.org/amhara-region-concerning-human-rights-violations-in-the-context-of-the-armed-conflict/

40. Foreign Policy (2024). Ethiopia's Amhara Conflict Could Spark Civil War. https://foreignpolicy.com/2024/03/06/ethiopia-amhara-conflict-civil-war/


41. Amnesty International (2024). Ethiopia: End extrajudicial Executions in Amhara region, bring perpetrators to justice. https://www.amnesty.org/en/latest/news/2024/02/ethiopia-end-extrajudicial-executions-in-amhara-region-bringperpetrators-to-justice/

42. Access Now (2022). After years in the dark, Tigray is slowly coming back online. https://www.accessnow.org/tigrayshutdown-slowly-coming-back-online/

43. See AP News (2024). Ethiopia's Tigray region is now peaceful, but extreme hunger afflicts its children. https://apnews.com/article/ethiopia-hunger-crisis-tigray-malnutrition-health-7e085f5bd2ac138a27fdc0ec544fb296/

## ኢ.አ.አ. በ 2023 የነበሩ የኢንተርኔት አገልግሎት መቋረጦች▼

- 5.9% ብቻ አንድ ከተማ፣ አንድ አገር ወይም መንደር ላይ የተደረገ የአገልግሎት መቋረጥ ነው
- 11.8% በአንድ ተመሳሳይ ግዛት፣ ክፍለ ሀገር ወይም ክልል ውስጥ ከአንድ ከተማ በላይ በሆኑ ላይ የተደረገ የአገልግሎት መቋረጥ ነው




## የመገናኛ አውታሮች እገዳ


በቀጣናው ከደረሱ 17 የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች ውስጥ በአሥሩ ባለሥልጣናቱ በተለይ የማኅበራዊ ሚዲያ አውታሮችን ነበር ዒላማ ያደረጉት። በኢትዮጵያና በሴኔጋል በተቀሰቀሱት ተቃውሞዎች እንዲሁም በጊኒ በተደረገው ምርጫ መንግሥታት የመረጃ ፍሰትን ለመገደብና የሐሳብ ልዩነቶችን ለመጨፍለቅ የማኅበራዊ ሚዲያ አውታሮችን ዘግተዋል። የኬንያ ባለሥልጣናት ደግሞ በኅዳር ወር ብሔራዊ ፈተና በተሰጠበት ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ ቴሌግራም ላይ እገዳ ጥለው ነበር።[44] ከመንግሥት ምንም ዓይነት ይፋዊ የሆነ የመዘጋት ትእዛዝ የተላለፈ ባይሆንም እገዳው የተጣለው ሾልከው የወጡ የፈተና ወረቀቶችን ስርጭት ለመገደብ ነው ተብሏል።[45]

የጋንዳ ከ2021 የምርጫ ወቅት ጀምሮ ፌስቡክን ማገዷ በሰብአዊ መብቶችና በዲጂታል ገበያ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱን ቀጥሏል።[46] ሆኖም በወርኀ ጥቅምት 2023 የከተማ ስማርት ነጋዴዎች ቢዝነስ ማኅበር የሕግ ማስፈራሪያ ካደረገ እንዲሁም በ2021 በምሥራቅ አፍሪካ የፍትሕ ፍርድ ቤት ያልተቋጨ ክስ ካቀረበ በኋላም መንግሥት እገዳውን ማንሣት አልቻለም።[47]

በጥር 2024 የዩጋንዳ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂና ብሔራዊ መመሪያ ሚኒስትር የዩጋንዳ ኮሙኒኬሽን ኮሚሽን (UCC) ከሦስት ዓመት እገዳ በኋላ በሀገሪቱ ውስጥ እንዴት ሥራ መጀመር እንዳለበት ከፌስቡክ ጋር እየተነጋገረ ነው ብለዋል። ነገር ግን ይህን ሪፖርት በምንጽፍበት ሰዓት የዚህ ንግግር ውጤት በእርግጠኝነት ምን እንደሆነ አይታወቅም።[48]

በታንዛኒያ ባለሥልጣናት ከ2020 በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ አገልግሎትን መሠረት ያደረጉ እገዳዎችን ጣሉ። እርምጃው በዲጂታል አውታሮች ላይ የሚወሰደው እርምጃ እየጨመረ መሄዱን የመላከተ ነው። በወርኀ ጥር ባለሥልጣናቱ የግሪንደር (Grindr) አገልግሎትን ያገዱ ሲሆን እርምጃው የLGBTQ+ ሰዎችና ማኅበረሰቦችን መብቶች የማፈን አካል ነበር።[49] በነሐሴ ወር ደግሞ ያለ ምንም ማብራሪያ ክለብ ሃውስ (Clubhouse) በተባለው የድምጽ መወያየ የማኅበራዊ ትስስር መተግበሪያ ላይ እገዳ ተጣለ።[50] ከጥቂት ወራት በኋላ የታንዛኒያ ኮሙኒኬሽን ቁጥጥር ባለሥልጣን (TCRA) ሰዎች የታገዱ መገናኛ አውታሮችን እንዳይጠቀሙ የሚያስችለውን ምናባዊ የግል ኔትወርክ (ቪፒኤን) መጠቀምን የሚገድብ መመሪያ አወጣ።[51]

44. Access Now (2023). Telegram in Kenya: keep people connected during national exams. https://www.accessnow.org/press-release/telegram-kenya-connected-national-exams/
45. TechCabal (2023). Telegram is disrupted in Kenya as internet authorities remain silent. https://techcabal.com/2023/11/21/telegram-offline-in-kenya/
46. Monitor (2022). We'll reopen Facebook when they stop playing games – Museveni. https://www.monitor.co.ug/uganda/news/national/we-ll-reopen-facebook-when-they-stop-playing-games-museveni-4064942
47. allAfrica (2023). Uganda: Govt Given Two Week Ultimatum to Reopen Facebook or Face Legal Action. https://allafrica.com/stories/202310250583.html; East African Court of Justice (2021). Reference No. 12 of 2021 East African Law Society v. The Attorney General of the Republic of Uganda & The Secretary General of the East African Community. https://www.eacj.org/?cases=reference-no-12-of-2021-east-african-law-society-v-the-attorney-general-of-the-republic-of-uganda-thesecretary-general-of-the-east-african-community
48. New Vision (2024). Govt, Facebook in talks to end three year blockade. https://www.newvision.co.ug/category/news/govt-facebook-in-talks-to-end-three-year-bloc-NV_179442/
49. OONI (2023). Tanzania blocked Grindr. https://explorer.ooni.org/findings/203466718601/
50. OONI (2023). Tanzania blocked Clubhouse. https://explorer.ooni.org/findings/185407756401/
51. CIO Africa (2023). Tanzania Imposes Ban On VPN Usage Without A Permit. https://cioafrica.co/tanzania-imposes-ban-onvpn-usage-without-a-permit/




# #KeepItOn

# የዲሞክራሲ መጥበብ፣ የሁከት መጨመር

## የ2023 የኢንተርኔት መዘጋት ክስተቶች

CC BY